# በአትላንታ የመነኩሴዉ

# ጽባቴ የማነ ብርሃን ቅሌት

ከሃይማኖት ፍጽም

በእኚህ መነኩሴ ምክንያት የቤተክርስቲያን ታሪክ የሚያጎድፍ የሥጋ ድክመት ችግሮች ተከስተዋል።

እነዚህ ችግሮች ሰፊ አሉባልታና ሐሜት ስለፈጠሩ ለቤተ-ክርስቲያኑ ብስራተ ቅዱስ ገብረኤል ኃላፊነት ያለዉ የአመራር አካል ልዩ ትኩረት ስጥቶ ሁሉን ነገር በተገቢዉ ማስረጃ በመመርመር ተወያይቷል። በዉይይቱም መሰረት በማስረጃ የተደረሰባቸዉ ጥፋቶች በወቅቱ የቤተክርስቲያኑ የበላይ ካህን መነኩሴ የሆኑት ጽባቴ የማነ ብርሃንን ጥፋተኛና ተጠያቂ አድርጋል። መነኩሴዉም የማነ ብርሃን አጠፋህ ተብለዉ የተጠየቁት ገዳዮች ሁሉ አንድም ሳይከዱ ጥፋታቸዉን በማመናቸዉና በራሳቸዉም እንደበት ድርብ ሕይወት የሥጋዊ አለም በድብቅ ለረዥም ጊዜ እንደኖሩ ተናዘዉ ከሥራ ተሰናብተዉ ከአንድ አመት በፊት ቤተክርስቲያኑን ለቀዉ ወደ ኢትዮጵያ እንድሄዱ ተደርጋል።

ነገር ግን በአልታወቀ ምክንያት በቅርብ ጊዜ ወደ አትላንታ ተመልሰዉ በመምጣት በብስራተ ቅዱስ ገብረኤል ቤተክርስቲያን ለመግባት ሞክረዉ ኣልተሳካላቸዉም። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ኮሚኒቲን በሬድዉ ፕሮፓጋንዳ የአሉባልታና ሐሜት፡- የብስራተ ቅዱስ ገብረኤል ቤተክርስቲያን የሰይጣን ማአበል ገብቶበታል በማለትና ምእመናኑን በሰይጣን ማስመሰልና የትአቢት፡- ማን አለብኝ ህዉከት በመፍጠር ሰላምን እየነሱ ይገኛሉ። አለማዊ መነኩሴዉ ራስን ስዩመ-እግዚኣብሔር ኣድርጎ እንደ እየሱስ ክርስቶስ እኔም እንዱ በግ ጠባቂ ነኝ ብሎ በመመጻደቅ የሀስት ተከታይ ለመፍጠር የጥላቻና የቂም በቀል ፕሮፓጋንዳ መናፍስታዊ ተግባር በመንዛት ኮሚኒቲዉን እያወኩ እጋንታዊ ሥራዉን ተያይዘዉታል። እኚህ አለማዊ መነኩሴ የአግዜአብሔርን መንገድ የሳቱ፡- የክርስትና ሃይማኖትን ያፈረሱ፡- ከፈተና የወደቁ፡-ንሥሃ መግባትን የማይፈልጉ፡- መናፍስታዊ ሥራ አራማጅ የሰይጣን ፈረስ ፡- የመንፈሳዊ ወንጀለኛ ናቸዉ። “ሰይጣን ለማሳሳት ቅዳሴ ያወርዳል” እንደተባለዉ ነዉ። እኚህ ሰዉዬ ክርስትና ሃይማኖታችን ላይ ችግር ከሚፈጥሩና ምእመናን ከምእመናን ማወዛገብን፡- ያልሆነ ዱስኩሩን ቢያቆሙና በቶሎ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዉ በኣባ ጳዉሎስ ጠበል ቢጠመቁ ለሁለቱም መልካም ፈዉስ ይገኛል እንላለን።

የመነኩሴ ተግባር፦ አኗኗር፦ ሥነ-ምግባር ወዘተ. በመጸሐፈ- መነኮሳት የተወሰነ ነው።የኚህ መነኩሴ ሥራ ከሠራዊተ -ጌታ፦ከሕያው አምላካችን ቅዱስ ቃል ትእዛዝ፦ ሕግ-ውጭ አምነቱን በመተላለፍ የሥጋ ምኞትና ፍላጎትን ለማርካት ሲባል የፈጸሙት ርኩስ ድርጊት ነው።

ማቴ 6-9" አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆን ውይንም ጣኦትን የሚያመልኩ ወይንም አመንዝሮች ወይንም ዝሙት የሚስሩ ወይንም ሌቦች ወይንም ገንዘብን የሚመኙ ወይንም ሰካራሞች ወይንም ተሳዳቢዎች ወይንም ነጣቂዎች የእግዜኣብሔርን መንግሥት አይወርስም"።

<u>በመሰረቱ መነኩሴ ማለት፦</u>

በመጸሐፈ-መነኮሳት ያሉትን ሥነ-ምግባራት ሥርአት የተከተለና የሚአከብር በምን ውስጥ የማይገባ፦

-ገንዘብ የማይሰበስብ

-የጣሙ፦የጣፈጠ፦ የላመ የምግብ አይነት የማይበላ።

-የራሱ የሆነ ቤት ንብረት የሌልው፦ በባዶ እግሩ የሚሄድ።

-የእግዜአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያደረበት ሰው ነው።

-ከመስቀል በስተቀር ምንም ነገር የማያስፈልገው ከዚህ አለም ጋር ግንኙነት የሌለው የሞተ ሰው ነው።-
-መነኩሴ በገዳም በአገር ውስጥ የሚኖር የሚጾም የሚጸልይ ነው። አይሰደድም።

ከዚህ ውጭ ያሉ መነኮሳት ልባቸው ያልመነኮሰ፦ ተግባራቸው የሥጋን ሥራዎች የተከተለ፦ ከአውነተኛ ምንኩስና ሥራ የወጡ ሲሆኑ የምንኩስና ልብሳቸው ቤተክርስቲያንን የሚያፈርስ ማጭበርበሪያ ነው።

በዚህ አንጻር ጸባቴ የማነ ብርሃን የመነኩሴን ሕገ-ምግባርና አኗኗር የማያሟሉ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ለሥጋ እያደሉ ለሐይማኖትና ለምእመናኑ መሪና አርአያ ሊሆኑ ባለመቻላቸው የሚከተሉትን ፈጽመዋል።

-የሥልጣን ጥመኛ ሆነዋል

-የራሳቸው የሆነ ቤት፦ ንብረት አትላንታና አዲስ ኣበባ ላይ ገዝተዋል

-ገንዘብ አግበስብሰዋል

-መነኩሴ ያሞተ ይህ አለም የበቃዉ ሲሆን እኚህ መነኩሴ ግን አለምን ወደዉ በሁሉ ነገር ዉስጥ እየገቡ ብዙ አዉከዋል።

-የምእመናንን አንድነትና ኅብረት በመጠበቅ ፈንታ በግልጽና በስዉር በመከፋፈል ቤተክርስቲያንን የሚያዳክም ብሎም የሚያፈርስ ሥራ ፈጽምዋል።

-ሴቶችን በመኖርያ ቤታቸዉ እያቀረቡ የጣሙ፦ የጣፈጡ፦ የላመ ምግብ እየተቀበሉ በመጠቀም ተገልግለዋል።

-በሥጋ ምኞት በመመራት መዳራትና ዝሙትነትን ፈጽመዋል።

-ጋብቻ እግዚአሔር የባረከዉ የሰዉ ልጆች የፍቅርና የሕይወት ትልቅ ሥራ ሲሆን አንዳንድ እንስታይት ምእመናንን በማስፈራራትና በጉልበት ልብስ ተጋፈዉ ትዳር እንድፈርስና ቤተሰብ እንድበተን አድርገዋል።

-ዝማዊ መነኩሴዉ በአካሄዱት መዳራት ምክንያት አንዳንድ ሴት ምእመናን በአጠቃላይ ሌሎችም ምእመናን ተግባሩን በመጥላት ቤተክርስቲያን እንድጠሉና እንድሸሹ ሆነዋል።

-ማኅበረ-ቅዱሳን መዘምራኑን እንዳለ እንድፈርስና እንድበተን ተደርጋል

-የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋህዶ ሃይማኖት የምትመራበትን ሕገ- ምግባርና ሥርአት አፍርሰዋል። ወዘተ.

የእኚህን የበግ ለምድ ለብሰዉ በረት ዉስጥ ያገቡ ተኩላ ስዉር ተንኮለኛ ማጋለጥና እንድታወቅ ማድረግ የጽኑ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች ሁሉ ኃላፊነትና ግደታ ነዉ። ዛሬ በአገራችን ኢትዮጵያና በሕዝባችን ላይ ያሉት ችግሮችና ፈተናዎች ያሳሰባቸዉ፦ ያስጨነቃቸዉ በዱር በገደሉ ቅጠል በልተዉ አፈር እየላሱ ቀን ከሌሊት በጾም በጸሎት አምላክን የሚማጸኑ መነኮሳትና ባህታዊያን ባሉባት አገር የአለማዊዉ መነኩሴ ታሪክና ሁኔታ እጂግ የሚገርምና የሚያሳዝነን ጉዳይ ሆኖል።

ይህ ዝማዊ መነኩሴ

-የመንኩስና ሥነ-ምግባርን ጥሳል

-የአሥርቱ ቃላትን ሕግጋት አፍርሷል

-ሃይማኖትና ሥነ- ምግባርን ተላልፋል

-የጋብቻ ደንብና ምግባር ተላልፏል ፦ተደፍሯል

-የክርስትና እምነት  በአጠቃላይ አፍርሷል

-ባሕላዊ ሥነ-ምግባር፦ ቤተሰባዊ ስአርትና ወግ ጎድቷል።

ስለዚህ ሁሉም የኘህን አለማዊ-ዝማዊ መነኩሴ ጥፋትና መጋለጥ አዉቆ ከሃስተኛ ፕሮፓጋንዳና መሰሪ ተንኮላቸዉን እንዲያወግዝ እያሳሰብን የክርስትና ሃይማኖት ተቆርቁሪ ሁሉና፦ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ቤትክርስቲያን የማእከላዊ አስተዳደር ይህን ጉዳይ ለቅዱስ ሲኖዶስ አቅርቦ ተገቢወን የርምት ርምጃ እንድወሰድና የክርስትና እምነታችን እንድጠበቅልን አደራ እንላለን።

02/03/2012